የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 58
ADDIS ABABA 22nd August, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬ ዓ.ም

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ……… ገጽ ፮ሺ፬፻፺፯

CONTENTS

**Proclamation No.760/2012**

Registration of Vital Events and National Identity Card Proclamation. …….Page 6497

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬

**ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ስለብሔራዊ መታወቂያ የወጣ አዋጅ**

የፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማቀድ፣ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ዜጎች ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ እና በፍትሕ አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

ወሳኝ ኩነቶችን ዜጎች በአግባቡና በወቅቱ እንዲያስመዘግቡ የሚያስችል ተደራሽ፣ ሁሉን አቀፍ እና አስገዳጅ የሆነ የምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የብሔራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግ ብሔራዊ መታወቂያ ለዜጎች መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፮) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷/፪ሺ፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 760/2012

**A PROCLAMATION ON THE REGISTRATION OF VITAL EVENTS AND NATIONAL IDENTITY CARD**

**WHEREAS,** establishing a system of registration of vital events plays a key role in planning political, social and economic developments, in providing different social and economic services to citizens and in making the justice administration expedient and effective;

**WHEREAS,** it has become necessary to create accessible, comprehensive and compulsory registration system on the basis of which citizens can effect proper and timely registration of vital events;

**WHEREAS,** the issuance of national identity cards to citizens has become important for the protection of national security, and for providing efficient services to citizens by the public and private sectors;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### CHAPTER ONE

### GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Registration of Vital Events and National Identity Card Proclamation No. 760/2012”.

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ “ወሳኝ ኩነት” ማለት ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺ ወይም ሞት ሲሆን ጉዲፈቻን፣ ልጅነትን መቀበል እና አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅን ይጨምራል፤

፪/ “የክብር መዝገብ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወሳኝ ኩነት መረጃዎች የሚመዘገቡበት መዝገብ ነው፤

፫/ “የክብር መዝገብ ሹም” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ወሳኝ ኩነትን እንዲመዘግብ የተመደበ ኃላፊ ነው፤

፬/ “አስመዝጋቢ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ወሳኝ ኩነትን የማስመዝገብ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፤

፭/ “መደበኛ መኖሪያ ቦታ” ማለት በፍትሐ ብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፩፻፹፫ እስከ አንቀፅ ፩፻፺፩ የተደነገገውን የሚያሟላ የአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቦታ ነው፤

፮/ “አግባብ ያለው የፌዴራል አካል” ማለት የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወይም ብሔራዊ መታወቂያ መስጠትን በሚመለከት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተቋቋመ አካል ነው፤

፯/ “አግባብ ያለው የክልል አካል” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የተቋቋመ ወይም የተሰየመ የክልል አካል ነው፤

፰/ “የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት” ማለት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የሚከናወንበት የክልል ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጽሕፈት ቤት ነው፤

፱/ “ብሔራዊ መለያ ቁጥር” ማለት አንድን ኢትዮጵያዊ ከሌሎች ግለሰቦች ለመለየት የሚያገለግል ቁጥር ነው፤

፲/ “ለአካለ መጠን መድረስ” ማለት የአስራ ስምንት ዓመት እድሜ መሙላት ሲሆን ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ መውጣትን ይጨምራል፤

፲፩/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፪/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡



## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ “vital event” means birth, marriage, divorce or death, and includes adoption, and acknowledgement and judicial declaration of paternity;

2/ “register of civil status” means a register wherein particulars of vital events are recorded in accordance with this Proclamation;

3/ “officer of civil status” means an officer assigned to register vital events in accordance with this Proclamation;

4/ “declarant” means a person who has the responsibility to declare a vital event for registration in accordance with this Proclamation;

5/ “principal residence” means the place where an individual resides that satisfies the provisions of Article 183 to Article 191 of the Civil Code;

6/ “appropriate federal organ” means an organ established by the Council of Ministers regulation with respect to the registration of vital events or the issuance of national identity card;

7/ “appropriate regional organ” means a regional organ established or designated pursuant to Article 5 of this Proclamation;

8/ “administrative office” means an office of a region's lowest level of administrative hierarchy where the registration of vital events carried out;

9/ “national identification number” means a number used to identify an Ethiopian from other individuals;

10/ “attainment of majority” means attainment of the age of eighteen years, and includes emancipation;

11/ “region” means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

12/ “person” means any natural or juridical person;

13/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ፡-

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በሚመለከት በማንኛውም ኢትዮጵያዊ፤ እና

፪/ ብሔራዊ መታወቂያን በተመለከተ ለአካለ መጠን በደረሰ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፤

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>የወሳኝ ኩነት መዝጋቢ አካላት</u>**

፬. **<u>የፌዴራል አካል</u>**

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባራትን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተባብርና የሚደግፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን በማዕከል አደራጅቶ የሚይዝ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል፡፡

፭. **<u>የክልል አካል</u>**

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ተግባራትን በክልል ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተባብርና የሚደግፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ላለው የፌዴራል አካል የሚያስተላልፍ አግባብ ያለው የክልል አካል በእያንዳንዱ ክልል የሚቋቋም ወይም የሚሰየም ይሆናል፡፡

፮. **<u>የክብር መዝገብ ሹም</u>**

፩/ ክልሎች ለእያንዳንዱ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም እንዲመደብ ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ የክብር መዝገብ ሹም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት፡-

ሀ) ወሳኝ ኩነቶችን ይመዘግባል፤

ለ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቅጂዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

ሐ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለሚመለከተው ሰው ይሰጣል፤

መ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ሚስጥራዊነታቸውንም ይጠብቃል፤

ሠ) ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያከናውናል፤

ረ) አግባብ ባለው የክልሉ አካል የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. **<u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall apply:

1/ to any Ethiopian with respect to the registration of vital events; and

2/ to any Ethiopian who has attained majority with respect to the issuance of national identity card.

**<u>CHAPTER TWO</u>**

**<u>REGISTRATION OF VITAL EVENTS</u>**

**<u>SECTION ONE</u>**

**<u>ORGANS FOR REGISTRATION OF VITAL EVENTS</u>**

4. **<u>Federal Organ</u>**

An appropriate federal organ shall be established by regulation of the Council of Ministers to direct, coordinate and support the registration of vital events at national level and to centrally organize and keep records of vital events.

5. **<u>Regional Organ</u>**

An appropriate regional organ shall be established or designated by each region to direct, coordinate and support the registration of vital events at regional level and to transfer records of vital events to the appropriate federal organ.

6. **<u>Officers of Civil Status</u>**

1/ Regions shall cause the assignment of an officer of civil status for each administrative office.

2/ An officer of civil status assigned pursuant to sub-article (1) of this Article shall, in accordance with the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder:

a) register vital events;

b) send copies of records of vital events to the relevant organs;

c) issue a certificate of registration of vital event to the concerned person;

d) properly preserve records of vital events and secure their confidentiality;

e) create awareness among the community on the registration of vital events;

f) carry out other functions assigned to him by the appropriate regional organ.

**፯. የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች**

፩/ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የቆንስላ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ወይም በአምባሳደሩ የሚመደብ የኤምባሲው ሠራተኛ እንደ ክብር መዝገብ ሹም በመሆን ይሠራል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት በሌለበት ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የሚመለከቱ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**፰. በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ስለሚከሰት ወሳኝ ኩነት**

፩/ በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ለሚከሰት ልደት ወይም ሞት መርከቡ እንደ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡ የመርከቡ ካፒቴንም እንደ ክብር መዝገብ ሹም በመሆን ይሠራል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ መርከብ ካፒቴን ከመርከቡ ሠራተኞች መካከል በየጉዞዉ ረዳት የክብር መዝገብ ሹም ሊመድብ ይችላል፡፡

**፱. በግዳጅ ላይ ያሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት**

፩/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በግዳጅ ላይ ባሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ የሚደርስ ሞት ምዝገባን በተመለከተ እንደ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር እንደ ክብር መዝገብ ሹም ሆኖ የሚሠራ ኃላፊ ይመድባል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለክብር መዝገብ**

**፲. የክብር መዝገብ ዓይነቶች**

እያንዳንዱ የወሳኝ ኩነት ዓይነት የተለየ የክብር መዝገብ ይኖረዋል፡፡

**፲፩. የክብር መዝገቦች አዘገጃጀት**

፩/ ማንኛውም የክብር መዝገብ በጥራዝ መልክ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

፪/ የክብር መዝገብ በቋሚነት ለማገልገል በሚያስችልና ለአያያዝ በሚያመች ሁኔታ ይዘጋጃል፡፡

፫/ የክብር መዝገብ ሽፋን የክብር መዝገቡ የሚመለከተውን የወሳኝ ኩነት ዓይነትና የምዝገባ ቦታውን የሚያመለክቱ መግለጫዎችን መያዝ አለበት፡፡

**7. Ethiopian Embassies and Consulates**

1/ The Ethiopian embassies and consulates shall serve as administrative office for Ethiopians residing in foreign countries; and the head of the consulate or an embassy staff assigned by the ambassador shall act as an officer of civil status.

2/ Registration of vital events with respect to Ethiopians residing in a country where there is no Ethiopian embassy or consulate shall be carried out in accordance with directive to be issued by the appropriate federal organ in consultation with the Ministry of Foreign Affairs.

**8. Vital Events on Board Ethiopian Ships**

1/ An Ethiopian ship shall serve as administrative office for the registration of birth or death that occurs on board; and the captain of the ship shall act as an officer of civil status.

2/ The captain of an Ethiopian ship may assign an assistant officer of civil status for each voyage from among the crew of the ship.

**9. Members of Defense Forces on Active Duty**

1/ The Ministry of National Defense shall serve as administrative office for registration of death of members of the defense forces on active duty.

2/ The Ministry of National Defense shall assign an officer that shall act as officer of civil status.

**SECTION TWO**

**REGISTER OF CIVIL STATUS**

**10. Types of Register of Civil Status**

Each type of vital event shall have a separate register of civil status.

**11. Preparation of Register of Civil Status**

1/ Any register of civil status shall be prepared in the form of a bound book.

2/ A register of civil status shall be prepared in a manner that ensures its durability and its convenience for handling.

3/ The cover page of a register of civil status shall contain a label indicating the particular type of vital event and the place of registration.

፬/ በክብር መዝገብ የሚሰፍሩ መረጃዎች በሚመለከተው ክልል የሥራ ቋንቋና በአማርኛ የሚፃፉ ይሆናሉ፡፡

## ፲፪. ስለክብር መዝገብ ቅጾችና ቅጅዎች

፩/ ማንኛውም የክብር መዝገብ ቅጽ አንድ ቀሪና ከዚሁ ቀሪ ጋር አንድ ዓይነት የሆኑ መረጃዎችን የያዙ ሦስት ቅጅዎች ይኖሩታል፡፡

፪/ የክብር መዝገብ ቅጽ ቅጅዎች ከዋናው ቅጽ ተለይተዉ ለሚመለከታቸው አካላት የሚላኩ ይሆናሉ፡፡

፫/ እያንዳንዱ ቅጽ ከነቅጅዎቹ ለአንድ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

፬/ የክብር መዝገብ የመጨረሻ ገጾች በክብር መዝገቡ ውስጥ የተመዘገቡትን ኩነቶች በአመዘጋገብ ቅደም ተከተል የሚያመለክት ማውጫ ይይዛሉ፡፡

፭/ እያንዳንዱ የክብር መዝገብ በህትመት ወቅት የራሱ የሆነ መለያ ኮድ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## ፲፫. የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ስርጭት

፩/ ለክልል የሚያገለግሉ የክብር መዝገቦች አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር አግባብ ባለው የክልሉ አካል ተዘጋጅተው ለሁሉም የአስተዳደር ጽህፈት ቤቶች ይሰራጫሉ፡፡

፪/ ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች፣ ለኢትዮጵያ መርከቦች እና ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚያገለግሉ የክብር መዝገቦች አግባብ ባለው የፌዴራል አካል ተዘጋጅተው ይሰራጫሉ፡፡

## ፲፬. የክብር መዝገቦችን ከቦታቸው ማዘዋወር የማይፈቀድ ስለመሆኑ

በሚመለከተው ባለሥልጣን ካልተፈቀደ በስተቀር የክብር መዝገብን ከተቀመጠበት የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ወደ ሌላ ቦታ ማዘዋወር የተከለከለ ነው፡፡

## ፲፭. ስለ ክብር መዝገቦች ደኅንነት አጠባበቅ

የክብር መዝገቦችን የመያዝ ኃላፊነት ያለበት አካል ለክብር መዝገቦቹ ደኅንነት አጠባበቅ ኃላፊ ይሆናል፡፡

4/ The information in a register of civil status shall be recorded in the official language of the concerned region and in Amharic.

## 12. Forms and Copies of Register of Civil Status

1/ Each registration form shall be accompanied by three detachable copies bearing identical particulars attached to a counterfoil.

2/ Copies of the record shall be detached from the main form and sent to the concerned organs.

3/ Each form, together with the copies, shall serve only for the registration of one vital event.

4/ The last page of a register of civil status shall contain an index showing the events registered according to their sequence.

5/ Each register of civil status shall be given an exclusive code during publication.

## 13. Preparation and Distribution of Registers of Civil Status

1/ Registers of civil status to be used by a region shall be prepared by the appropriate regional organ in collaboration with the appropriate federal organ and be dispatched to all administrative offices.

2/ Registers of civil status to be used by the Ethiopian embassies and consulates, Ethiopian ships and the Ministry of National Defense shall be prepared and distributed by the appropriate federal organ.

## 14. Restriction to Remove Register of Civil Status

A register of civil status may not be removed from the administrative office where it is kept unless authorized by the concerned official.

## 15. Safeguarding Registers of Civil Status

The organ entrusted to keep registers of civil status shall be responsible for their safeguarding.

፲፮. **ስለክብር መዝገብ መጥፋት፣ መውደምና መበላሸት**

፩/ የክብር መዝገብ የጠፋ፣ የወደመ ወይም የተበላሸ እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ መሠረት ለሚመለከተው አካል የተላለፉ ቅጂዎችን በመጠቀም መዝገቡን መልሶ ማደራጀት አለበት፡፡

፪/ በሚመለከተው አካል ዘንድ የተቀመጠ የምዝገባ ቅጽ ቅጅ የጠፋ፣ የወደመ ወይም የተበላሸ እንደሆነ ከክብር መዝገቡ ሌላ ቅጅ በመውሰድ መተካት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የወል ድንጋጌዎች

፲፯. **መርህ**

፩/ ማንኛውም ወሳኝ ኩነት ለሕጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታትስቲክስ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን በያዘ መልኩ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ወሳኝ ኩነት ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ የለበትም፡፡

፫/ ማንኛውም አስመዝጋቢ ወሳኝ ኩነትን ለማስመዝገብ በክብር መዝገብ ሹም ፊት በአካል መቅረብ አለበት፡፡

፬/ የክብር መዝገብ ሹሙ ስለወሳኝ ኩነቱና ተዛማጅ መረጃዎች በክብር መዝገብ ቅጽ ላይ ካሰፈረ በኋላ ስለተመዘገበው መረጃ ትክክለኛነት አስመዝጋቢው እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለበት፡፡

፲፰. **ስለምዝገባ ጊዜ**

፩/ ከልደት በስተቀር ማንኛውም ወሳኝ ኩነት ሊያዘገይ የሚያስችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በ፴ ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ልደት ሊያዘገይ የሚያስችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በ፺ ቀናት ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈፀመ እንደሆነ አስመዝጋቢው የዘገየበትን ምክንያት በማስረጃ ማስደገፍ አለበት፡፡

16. **Loss, Destruction and Damage of Register of Civil Status**

1/ Where a register of civil status is lost, destroyed or damaged, the officer of civil status shall recompile the register by using copies of the registration forms transferred to the relevant organ in accordance with Article 45 of this Proclamation.

2/ Where a copy of registration form deposited with the relevant organ is lost, destroyed or damaged, it shall be replaced by another copy taken from the register of civil status.

## SECTION THREE

## PROCEDURES OF REGISTRATION OF VITAL EVENTS

## SUB-SECTION ONE
## COMMON PROVISIONS

17. **Principle**

1/ Any vital event shall be registered with necessary detail information that can be used for legal, administrative and statistical purposes.

2/ No vital event may be registered more than once.

3/ A declarant shall appear in person before an officer of civil status to have a vital event registered.

4/ The officer of civil status, after entering the vital event and related information in the register of civil status, shall cause the declarant to confirm the information as it appears in the register.

18. **Period of Registration**

1/ Any vital event, other than birth, shall be registered within 30 days following the date of its occurrence unless there is sufficient cause for delay.

2/ Any birth shall be registered within 90 days following the date of its occurrence unless there is sufficient cause for delay.

3/ Where the registration of a vital event is not effected within the period specified under sub-article (1) or (2) of this Article the declarant shall produce evidence to justify the delay.

## ፲፱. የመረጃዎች አመዘጋገብ

፩/ ማንኛውም ወሳኝ ኩነት የሚመዘገበው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፫ መሠረት ተዘጋጅቶ በተሰራጨ የክብር መዝገብ ላይ ይሆናል፡፡

፪/ በክብር መዝገብ የሚሰፍሩ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች በተዘጋጀው የመመዝገቢያ ቅጽ ክፍት ቦታ ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡

፫/ የወሳኝ ኩነት መረጃዎችን ለመመዝገብ በጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላት ግልፅ የሆኑና ምንም ዓይነት ምህጻረ-ቃል፣ ስርዝ፣ ድልዝ ወይም ተጨማሪ ቃል ያልተደረገባቸው መሆን አለባቸው፡፡

## ፳. ክልከላ

በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጣ መመሪያ ተለይተዉ ከተመለከቱት መረጃዎች በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ቃል በክብር መዝገብም ሆነ በቅጾቹ ላይ መጻፍ የተከለከለ ነው፡፡

## ፳፩. ቅጾችን ስለመሰረዝ

የምዝገባ ቅጽ በስህተት ሳይሰራበት የተዘለለ እንደሆነ ወይም በስርዝ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት አንድ ምዝገባ እንደገና መከናወን ያለበት ከሆነ ቅጹ መስቀለኛ የሆኑ ሁለት መስመሮች ተደርገውበት ይሰረዛል፡፡ በጀርባው ላይም "ያልተሰራበት ቅጽ" የሚል ሀረግ ይጻፍበታል፡፡

## ፳፪. የተመዘገቡ መረጃዎችን ስለማረጋገጥና ስለማጽደቅ

፩/ የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺ ወይም የሞት አስመዝጋቢ በክብር መዝገቡ ላይ ስለሰፈሩት መረጃዎች ትክክለኛነት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ልጅነትን በፈቃደኝነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው በክብር መዝገቡ ስለሰፈረው መረጃ ትክክለኛነት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ጉዲፈቻ አድራጊ የሆነ ማንኛውም ሰው በክብር መዝገቡ ስለሰፈረው መረጃ ትክክለኛነት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የክብር መዝገብ ሹሙ ምዝገባው የተሟላ መሆኑን በመጨረሻ አረጋግጦ በመፈረም የወሳኝ ኩነት ምዝገባውን ማጽደቅ አለበት፡፡

## ፳፫. ስለፊርማ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት በክብር መዝገብ የሰፈሩ መረጃዎችን በፊርማው ማረጋገጥ ያለበት ሰው መፈረም የማይችል ከሆነ በፊርማው ፋንታ የጣት አሻራውን በምዝገባ ቅጹ ላይ ማድረግ አለበት፡፡



## 19. Entering of Particulars

1/ Any vital event shall be registered in the register of civil status prepared and distributed in accordance with Article 13 of this Proclamation.

2/ Particulars of a vital event shall be entered in the blank spaces provided in a registration form of the register of civil status.

3/ The words used to enter particulars of vital events shall be written clearly and without abbreviation, erasure, words written over others or any other additional word.

## 20. Prohibition

No words other than the particulars specifically provided for in this Proclamation or directive issued hereunder may be entered on the forms of a register of civil status.

## 21. Voiding Forms

If, as a result of a mistake, a form has been left unutilized or if, on account of erasure or for any other cause, a recording has to be redone, the form shall be cancelled by drawing two diagonal lines forming a cross; and the phrase "Form not Utilized" shall be written on its backside.

## 22. Confirmation and Approval of Records

1/ A declarant of birth, marriage, divorce or death shall confirm, by signing, the validity of particulars entered in the register of civil status.

2/ Any person who has acknowledged his paternity shall confirm, by signing, the validity of particulars entered in a register of civil status.

3/ Any person who adopted a child shall confirm, by signing, the validity of particulars entered in the register of civil status.

4/ The officer of civil status shall finally approve, by signing, the registration of a vital event upon ascertaining the completeness of the records.

## 23. Signature

If a person required to confirm the particulars entered in a register of civil status in accordance with Article 22 of this Proclamation cannot sign, he shall affix on the registration form his finger print instead of signature.

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለልደት ምዝገባ

### ፳፬. የልደት ምዝገባ ይዘት

የልደት ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የህፃኑን ሙሉ ስም፣ ፆታ፣ የተወለደበትን ቀን፣ የትውልድ ቦታ፣ የልደቱን ዓይነት (ነጠላ ወይም ከአንድ በላይ) እና በልደት ጊዜ የተደረገ እርዳታ፤

፪/ የህፃኑን ወላጆች ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ ብሔር እና ወላጆቹ በህይወት ካሉ ፊርማቸውን፤

፫/ አስመዝጋቢው የህፃኑ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ የአስመዝጋቢው ሰው ሙሉ ስም፣ ከህፃኑ ጋር ያለውን ዝምድና፣ ፆታ፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታና ፊርማ፤

፬/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ማኅተምና የምዝገባውን ቀን፤ እና

፭/ አግባብ ባለው የፌዴራል አካል የሚወሰኑ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፡፡

### ፳፭. ተጥሎ የተገኘ ህፃን ልደት ምዝገባ ይዘት

ተጥሎ የተገኘ ህፃን ልደት ምዝገባ፡-

፩/ ህፃኑ የተሰጠውን ስም፣ ፆታ፣ ይሆነዋል ተብሎ የሚገመተውን ዕድሜና የተገኘበትን ቀንና ቦታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎችን፤ እና

፪/ በምዝገባ ቅጹ ጀርባ ላይ "ተጥሎ የተገኘ" የሚል መግለጫ፤

መያዝ አለበት፡፡

### ፳፮. ልደትን የማስመዝገብ ግዴታ

፩/ የህፃኑ አባት ወይም እናት፣ ወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ የህፃኑ አሳዳሪ ወይም አሳዳሪ ከሌለ ህፃኑን በመንከባከብ ላይ ያለው ሰው ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ህፃኑ ተጥሎ የተገኘ ወይም ወላጆቹ የማይታወቁ የሆነ እንደሆነ ይህንን ሁኔታ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም አግባብ ላለው ለሌላ የመንግሥት አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## SUB-SECTION TWO

## REGISTRATION OF BIRTH

### 24. Particulars of Records of Birth

The records of birth shall contain the following particulars:

1/ the child's full name, sex, date of birth, place of birth, type of birth (whether single or more) and aid rendered during birth;

2/ the child's parents full name, date and place of birth, principal residence, marital status, citizenship, religion, ethnic origin and, if they are alive, their signatures;

3/ where the declarant is other than the parent of the child the declarant's full name, relation with the child, sex, date and place of birth, principal residence and signature;

4/ name and signature of the officer of civil status, seal of the administrative office and date of registration; and

5/ other necessary information as may be determined by the appropriate federal organ.

### 25. Particulars of Records of Birth of Abandoned Child

The records of birth of an abandoned child shall contain:

1/ the name given to the child, sex and estimated age of the child and the date and place where the child was found; and

2/ a phrase "abandoned child" on the backside of the registration form.

### 26. Obligation to Declare Birth

1/ The birth of a child shall be declared by the father or mother of the child, in their default, by the guardian of the child or, in default of guardian, by the person who has taken care of the child.

2/ Where the child is abandoned or his parents are unknown, any person who knows such condition shall have the duty to report same to the nearest police or other relevant government organ.

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሪፖርት የደረሰው ፖሊስ ወይም ማንኛውም ሌላ የመንግስት አካል በሦስት ቀን ውስጥ በአቅራቢያው በሚገኘው የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ቀርቦ ልደቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

## ፳፯. ስለህፃኑ ስም

፩/ የክብር መዝገብ ሹሙ ልደትን ከመመዝገቡ በፊት ህፃኑ የተሰጠዉን ወይም ሊሰጠው የታሰበዉን ስም አስመዝጋቢውን መጠየቅ አለበት፡፡

፪/ ለህፃኑ የተሰጠው ስም ለክብር መዝገብ ሹሙ ያልተነገረው እንደሆነ ወይም የተሰጠው የግል ስም ሕግን ወይም ልማድን የሚቃረን እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ የህፃኑን የግል ስም ማውጣት አለበት፡፡

## ፳፰. ስለልደት ምዝገባ ቦታ

፩/ የልደት ምዝገባ ቦታ በህፃኑ ወላጆች መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

፪/ ተጥሎ የተገኘ ወይም ወላጁ ያልታወቀ ህፃን የልደት ምዝገባ ቦታ ህፃኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

## ፳፱. በጤና ተቋም ውስጥ ስለተወለደ ህፃን

ልደቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ውስጥ የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱትን አግባብ ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ምስክር ወረቀት ወዲያውኑ አዘጋጅቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ መሠረት ልደቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰው መስጠት አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለጋብቻ ምዝገባ

## ፴. ስለጋብቻ ምዝገባ ይዘት

የጋብቻ ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የተጋቢዎችን ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ዜግነት፣ ብሔርና ሃይማኖት፤

፪/ ጋብቻው የተከናወነበትን ቀን፣ ቦታና ሥርዓት፤

፫/ የተጋቢዎቹን ፊርማ፤

3/ A police officer or any other government organ which has received a report in accordance with sub-article (2) of this Article shall have the duty to declare the birth to the officer of civil status of the nearest administrative office within three days from the date of receipt of the report.

## 27. Name of a Child

1/ The officer of civil status, prior to the registration of birth, shall enquire the name given or intended to be given to the child from the declarant.

2/ Where the name of the child is not disclosed or the name given is contrary to the law or custom, the officer of civil status shall himself choose a name for the child.

## 28. Place of Registration of Birth

1/ The place of registration of birth of a child shall be the nearest administrative office to the principal residence of the parents.

2/ The place of registration of birth of an abandoned child or child whose parents are unknown shall be the nearest administrative office to the place where the child was found.

## 29. Birth in a Health Institution

Where birth takes place in a health institution, the head of the institution shall forthwith prepare a certificate containing the relevant particulars specified under sub-article (1) and (2) of Article 24 of this Proclamation and give such certificate to the person having the duty to declare the birth in accordance with Article 26 of this Proclamation.

## SUB-SECTION THREE
## REGISTRATION OF MARRIAGE

## 30. Particulars of Records of Marriage

The records of marriage shall contain the following particulars:

1/ the couples' full name, date and place of birth, principal residence, citizenship, ethnic origin and religion;

2/ the date, place and form of the marriage;

3/ the couples' signature;

፬/ እንደሁኔታው ጋብቻው ስለመፈጸሙ የቀረበ ማስረጃ ወይም የሰው ምስክሮች ስምና መደበኛ መኖሪያ ቦታ፤

፭/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ማኅተምና የምዝገባውን ቀን፤ እና

፮/ አግባብ ባለው የፌዴራል አካል የሚወሰኑ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡፡

## ፴፩. ጋብቻን የማስመዝገብ ግዴታ

፩/ ጋብቻው የተፈፀመው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ጋብቻው በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ የተመለከተውን ማስረጃ ለክብር መዝገብ ሹም አቅርበው ጋብቻውን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

## ፴፪. የጋብቻ ምዝገባ ቦታ

የጋብቻ ምዝገባ ቦታ ተጋቢዎች በጋራ የሚወስኑት ቦታ፣ ከተጋቢዎቹ አንዱ ይኖርበት የነበረው ቦታ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንደኛው ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች የሚኖሩበት መደበኛ መኖሪያ ቦታ ይሆናል፡፡

## ፴፫. በሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሥርዓት የተፈጸመ ጋብቻ ማስረጃ

ጋብቻው የተፈፀመው በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት መሠረት ከሆነ፡-

፩/ የተጋቢዎቹን ስም፣ ዕድሜና መደበኛ መኖሪያ ቦታ፤

፪/ ጋብቻው የተፈጸመበትን ቀንና ቦታ፤ እና

፫/ የምስክሮችን ስም እና መደበኛ መኖሪያ ቦታ፤

የያዘ የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻውን ባስፈፀመው የሃይማኖት ተቋም ወይም ጋብቻውን ባስፈጸሙት ሽማግሌዎች ለተጋቢዎቹ ወዲያውኑ መሰጠት አለበት፡፡

4/ the evidence or the names and principal residences of witnesses of the marriage, as the case may be;

5/ name and signature of the officer of civil status, seal of the administrative office and date of registration; and

6/ other necessary information as may be determined by the appropriate federal organ.

## 31. Obligation to Declare Marriage

1/ Where marriage is celebrated before an officer of civil status, the officer of civil status who observed the marriage ceremony shall immediately register the marriage.

2/ Where marriage is celebrated by religious or customary ceremony, the couples shall present to an officer of civil status, for registration, the evidence of the marriage referred to in Article 33 of this Proclamation.

## 32. Place of Registration of Marriage

The place of registration of marriage shall be the place where the couples have jointly decided, the place where either of the couples had used to reside or the principal residence of the parents or close relative of either of the couples.

## 33. Evidence of Religious or Customary Marriage

Where the marriage is celebrated by a religious ceremony or customary practice, the religious institution or the elders who have observed the marriage shall immediately provide the couples with evidence of the marriage containing the following:

1/ the names, ages and principal residences of the couples;

2/ the date and place of the marriage; and

3/ the names and principal residences of the witnesses.

## ንዑስ ክፍል አራት

## ስለፍቺ ምዝገባ

**፴፬. የፍቺ ምዝገባ ይዘት**

የፍቺ ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የተፋቺዎቹን ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ዜግነት፣ ብሔርና ሃይማኖት፤

፪/ ጋብቻው የተፈፀመበትን ቀንና ቦታ እና ፍቺው የተፈፀመበትን ቀን፤

፫/ ስለፍቺው መፈፀም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሚያመለክት መግለጫ፤

፬/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ማህተምና የምዝገባውን ቀን፤ እና

፭/ አግባብ ባለው የፌዴራል አካል የሚወሰኑ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፡፡

**፴፭. ፍቺን የማስመዝገብ ግዴታ**

ተፋቺዎች በጋራ ወይም ከተፋቺዎቹ አንዱ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተወሰነ የፍቺ ውሳኔን ለክብር መዝገብ ሹም በማቅረብ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፰ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ፍቺውን ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

**፴፮. የፍቺ ምዝገባ ቦታ**

የፍቺ ምዝገባ ቦታ ፍቺው በተፈጸመበት አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

**፴፯. የፍቺ ማስረጃ**

የፍቺ ውሳኔ የሰጠ ማንኛውም ፍርድ ቤት የውሳኔውን ቅጅ ለተፋቺዎቹ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## ስለሞት ምዝገባ

**፴፰. የሞት ምዝገባ ይዘት**

የሞት ምዝገባ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

፩/ የሟችን ሙሉ ስም፣ ማእረግ፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ሥራ፣ መደበኛ መኖሪያ፣ ዜግነት፣ ብሔርና ሃይማኖት፤



## SUB-SECTION FOUR

## REGISTRATION OF DIVORCE

**34. Particulars of Records of Divorce**

The records of divorce shall contain the following particulars:

1/ the full name, date and place of birth, principal residence, citizenship, ethnic origin and religion of each divorcing partner;

2/ the date and place of conclusion of the marriage and the date of divorce;

3/ a reference to the decision of the competent court on the divorce;

4/ the name and signature of the officer of civil status, the seal of the administrative office and date of registration; and

5/ other necessary information as may be determined by the appropriate federal organ.

**35. Obligation to Declare Divorce**

The divorcing partners or one of them shall present the decision of the competent court on the divorce to an officer of civil status for registration of the divorce within the period specified under sub-article (1) of Article 18 of this Proclamation.

**36. Place of Registration of Divorce**

The place of registration of divorce shall be the nearest administrative office to the place where the divorce took place.

**37. Evidence of Divorce**

Any court which has rendered decision on divorce shall forthwith provide copies of the decision to the divorcing partners.

## SUB-SECTION FIVE

## REGISTRATION OF DEATH

**38. Particulars of Records of Death**

The records of death shall contain the following particulars:

1/ the full name, title, sex, age, occupation, principal residence, citizenship, ethnic origin and religion of the deceased;

፪/ የሞቱን ቀን፣ ቦታ፣ ምክንያትና ካለም ሞቱን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ የሚያመለክት መግለጫ፣

፫/ የክብር መዝገብ ሹሙን ስምና ፊርማ፣ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቱን ማህተምና የምዝገባውን ቀን፤ እና

፬/ አግባብ ባለው የፌዴራል አካል የሚወሰኑ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፡፡

## ፴፱. <u>ሞትን የማስመዝገብ ግዴታ</u>

፩/ ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች፣ እነዚህ የሌሉ እንደሆነ የቅርብ ጎረቤት ወይም ስለሟቹ መሞት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፫/ በአደጋ ወይም ባልታወቀ ምክንያት ሞቶ ማንነቱ ስላልታወቀ አስክሬን ሪፖርት የተቀበለ ፖሊስ ሪፖርቱ ከደረሰው ቀን በኋላ ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

## ፵. <u>በግዳጅ ላይ ስላለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሞት</u>

የመከላከያ ሠራዊት አባል በግዳጅ ላይ እያለ ከሞተ የክፍሉ አዛዥ በአገር መከላከያ ሚኒስቴር እንደ ክብር መዝገብ ሹም እንዲሠራ ለተመደበው ኃላፊ ሞቱን በማሳወቅ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## ፵፩. <u>በጋራ መኖሪያ ሥፍራ፣ በማረሚያ ቤት ወይም በጤና ተቋም ስለተከሰተ ሞት</u>

፩/ ሞቱ የተከሰተው በአዳሪ ትምህርት ቤት ወይም በሌላ የጋራ መኖሪያ ስፍራ የሆነ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ በአምስት ቀን ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ሞቱ የተከሰተው በማረሚያ ቤት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ወይም የሞት ቅጣት ፍርድ የተፈጸመ እንደሆነ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ በአምስት ቀን ውስጥ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፫/ ሞቱ የተከሰተው በጤና ተቋም ውስጥ ከሆነ ወይም አስክሬን ለምርመራ ወደ ጤና ተቋሙ የመጣ እንደሆነ የተቋሙ ኃላፊ የሟችን ስም፣ ፆታና የትውልድ ቀን፣ የሞተበትን ቀን፣ ቦታና ምክንያት እና የመሳሰሉ መረጃዎችን የያዘ የሞት ምስክር ወረቀት ወዲያውኑ በማዘጋጀት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ መሠረት ሞቱን የማስመዝገብ ግዴታ ላለበት ሰው መስጠት አለበት፡፡



2/ date, place and cause of the death and a reference to evidence of the death, if any;

3/ the name and signature of the officer of civil status, the seal of the administrative office and date of registration; and

4/ other necessary information as may be determined by the appropriate federal organ.

## 39. <u>Obligation to Declare Death</u>

1/ Any person who used to live with the deceased shall declare the death for registration.

2/ In the absence of persons used to live with the deceased, his relatives by consanguinity or affinity, close neighbors or any person who knows his death shall declare the death for registration.

3/ Any police which has received a report on the death of a person by accidental or unknown cause and whose identity is not known shall declare the death for registration within three days following the date of receipt of the report.

## 40. <u>Death of Member of Defense Force on Active Duty</u>

The death of a member of defense force on active duty shall be declared, for registration, by the commanding officer of his unit to the officer assigned by the Ministry of National Defense to act as an officer of civil status.

## 41. <u>Death Occurring in Common Dwelling Place, Prison or Health Institution</u>

1/ If a person dies in a boarding school or in any other common dwelling place, the person who is in charge of such institution shall declare the death for registration within five days.

2/ If a person dies in prison or if a death sentence is executed, the head of the prison shall declare the death for registration within five days.

3/ Where a death occurs in a health institution or a corpse is brought to it for examination, the head of the institution shall forthwith prepare a certificate of death containing the name, sex and date of birth of the deceased, the date, place and cause of death and other related information and give the certificate to the person having the responsibility of declaring the death for registration pursuant to Article 39 of this Proclamation.

## ፵፪. በአደጋ ምክንያት ስለሞቱ ብዙ ሰዎች

በአደጋ ምክንያት ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ሲሞቱ አደጋው ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል ከአደጋው በኋላ ሊገኝ ያልቻለ ሰው ስለአደጋው መከሰትና የጠፋው ሰው በአደጋው ወቅት ከተጎጂዎቹ ጋር አብሮ የነበረ ስለመሆኑ ባጣራው አካል የተሰጠ ማስረጃ ሲቀርብ መሞቱ ይመዘገባል፡፡

## ፵፫. ስለሞት ምዝገባ ቦታ

፩/ የሞት ምዝገባ ቦታ በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

፪/ ማንነቱ ወይም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ለማይታወቅ ሟች የሞት ምዝገባ ቦታ አስክሬኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩(፩) መሠረት የሚፈጸም የሞት ምዝገባ ቦታ በአስመዝጋቢው ተቋም አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡

## ፵፬. ስለመጥፋት

፩/ ማንኛውም ሰው የጠፋን ሰው በሚመለከት አግባብ ባላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አመልክቶ ስለመጥፋቱ ወይም ስለመሞቱ ውሳኔ ያሰጠ እንደሆነ የውሳኔውን ግልባጭ በጠፋው ሰው የመጨረሻው መደበኛ መኖሪያ ቦታ አቅራቢያ ለሚገኘው የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት የክብር መዝገብ ሹም አቅርቦ ሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመዘገበ ሞትን የሚመለከት የመጥፋት ውሳኔን የሚሽር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ሌላ ውሳኔ ለክብር መዝገብ ሹሙ የደረሰው እንደሆነ የቀድሞው የሞት ምዝገባ መሰረዝ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

### የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቅጂዎች እና የምስክር ወረቀት

## ፵፭. የምዝገባ ቅጂዎችን ስለማስተላለፍ

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የክብር መዝገብ ሹሙ የምዝገባ ቅጹን ሦስት ቅጂዎች አግባብ ላለው የክልሉ አካል መላክ አለበት፡፡

## 42. Death of Several Persons by Calamity

Where several persons die simultaneously due to a calamity, the death of a person who disappeared thereafter shall be registered upon presentation of evidence issued by the organ that have investigated the occurrence of the calamity and the presence of that person among the victims during the calamity.

## 43. Place of Registration of Death

1/ The place of registration of death shall be the nearest administrative office to the principal residence of the deceased.

2/ Where the identity or principal residence of the deceased is unknown, the place of registration of death shall be the nearest administrative office to the place where his corpse was found.

3/ The place of registration of death referred to in Article 41(1) of this Proclamation shall be the nearest administrative office to the institution declaring the death.

## 44. Absence

1/ Any person who has, upon lodging an application to the competent court in accordance with the relevant provisions of the Civil Code, obtained a judicial declaration on the absence or death of a person shall present the copy of the judgment, for registration of death, to the officer of civil status of the nearest administrative office to the last principal residence of the person whose absence or death has been declared.

2/ The records of death entered in accordance with sub-article (1) of this Article shall be cancelled where the officer of civil status receives another judgment rendered by a competent court revoking the previous judgment declaring absence.

## SECTION FOUR

### COPIES AND CERTIFICATE OF REGISTRATION OF VITAL EVENT

## 45. Transfer of Copies of Records

1/ Where the registration of a vital event is completed, the officer of civil status shall send three copies of the registration form to the appropriate regional organ within 30 days following the date of registration.

፪/ አግባብ ያለው የክልሉ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከደረሱት የምዝገባ ቅጽ ቅጂዎች ሁለቱን በደረሱት በ፴ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መላክ አለበት፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ባጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ሦስት ቅጂዎች ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

፬/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ከደረሱት የምዝገባ ቅጽ ቅጂዎች ሁለቱን በደረሱት በ፲ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መላክ አለበት፡፡

፭/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር እያንዳንዱን በግዳጅ ላይ ያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሞት ምዝገባ ቅጽ ሁለት ቅጅዎችን አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መላክ አለበት፡፡

፮/ የኢትዮጵያ መርከብ ካፒቴን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ የምዝገባ ቅጹን ሁለት ቅጂዎች አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መላክ አለበት፡፡

፯/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት ከደረሱት የምዝገባ ቅጽ ቅጂዎች አንዱን በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መላክ አለበት፡፡

፵፮. **<u>የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት አዘገጃጀት</u>**

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መሠረት በክብር መዝገብ ላይ የሰፈሩትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

፪/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በሚመለከተው ክልል የሥራ ቋንቋና በአማርኛ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

፵፯. **<u>የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

፩/ የልደት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ልደቱን ላስመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

፪/ የጋብቻ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ ለተጋቢዎች ለእያንዳንዳቸው ይሰጣል፡፡

፫/ የፍቺ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ ለተፋቺዎች ለእያንዳንዳቸው ይሰጣል፡፡



2/ The appropriate regional organ shall send two of the copies of the registration form it has received in accordance with sub-article (1) of this Article to the appropriate federal organ within 30 days following the date of receipt.

3/ An Ethiopian embassy or consulate shall send three copies of the registration form to the Ministry of Foreign Affairs within 30 days following the date of completion of the registration of a vital event.

4/ The Ministry of Foreign Affairs shall send two of the copies it has received in accordance with sub-article (3) of this Article to the appropriate federal organ within 10 days following the date of receipt.

5/ The Ministry of National Defense shall send two copies of the registration form of the death of a member of defense force on active duty to the appropriate federal organ.

6/ The captain of an Ethiopian ship shall send two copies of the registration form to the appropriate federal organ within 30 days following the date of completion of the registration of a vital event.

7/ The appropriate federal organ shall send one of the copies of a registration form it has received in accordance with this Article to the Central Statistics Agency within 30 days following the date of receipt.

46. **<u>Preparation of Certificate of Registration of Vital Events</u>**

1/ A certificate of registration of vital events shall contain the particulars entered in the register of civil status pursuant to the relevant provisions of this Proclamation.

2/ Certificate of registration of vital events shall be prepared in the official language of the concerned region and in Amharic.

47. **<u>Issuing Certificate of Registration of Vital Events</u>**

1/ A certificate of registration of birth shall be given to the person who has declared the birth in accordance with this Proclamation.

2/ A certificate of registration of marriage shall be prepared in two copies and be given to each spouse.

3/ A certificate of registration of divorce shall be prepared in two copies and be given to each divorcing partner.

፬/ የሞት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት ሞቱን ላስመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

፭/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ይሆናል፡፡

፮/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው አግባብ ያለውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም ምትክ የምስክር ወረቀት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

**፵፰. የማስረጃነት ክብደት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ መሠረት በተሰጠ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በክብር መዝገቡ ላይ ከሰፈሩት መረጃዎች ጋር እኩል የማስረጃነት ክብደት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የክብር መዝገብ መረጃዎችን ስለማረም

**፵፱. የአጻጻፍ ስህተትን ስለማረም**

፩/ የክብር መዝገብ ሹም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ጥያቄ መሠረት የክብር መዝገብ መረጃዎችን የሚመለከት የአፃፃፍ ስህተትን ያርማል፡፡

፪/ እርማቱ የቃል ወይም ቁጥር መሰረዝን የሚያስከትል የሆነ እንደሆነ ቃሉ ወይም ቁጥሩ ከተሰረዘም በኋላ በሚነበብበት ሁኔታ ይሠረዛል፡፡

፫/ እርማቱ የምዝገባ ቅጹ ቅጅዎችንም የሚመለከት ሲሆን የክብር መዝገብ ሹሙ ስለእርማቱ ቀደም ሲል ቅጅዎቹ ለደረሷቸው አካላት ሁሉ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፶. ሌሎች እርማቶች**

በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተመሥርቶ ካልሆነ በስተቀር ከአፃፃፍ ስህተት ውጭ የሆኑ በክብር መዝገብ ውስጥ የሰፈሩ መረጃዎችን የሚመለከቱ ሌሎች እርማቶችን ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

**፶፩. የእርምት ጥያቄ ስለማቅረብ**

በክብር መዝገብ የሰፈረ መረጃ እንዲታረም በዐቃቤ ሕግ፣ በክብር መዝገብ ሹም ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም ሰው ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡



4/ A certificate of registration of death shall be given to the person who has declared the death in accordance with this Proclamation.

5/ A certificate of registration of vital event shall be issued upon payment of service fee prescribed by regulation issued hereunder.

6/ Any person whose certificate of registration of vital event is lost or damaged shall have the right to get a replacement certificate upon payment of the prescribed service fee.

**48. Probative Value**

The certificate of registration issued in accordance with Article 47 of this Proclamation shall have equal probative value as the records of the register of civil status.

## SECTION FIVE

## CORRECTION OF RECORDS OF REGISTER OF CIVIL STATUS

**49. Clerical Mistakes**

1/ The officer of civil status shall, at the request of an interested party, make corrections involving clerical mistakes in the particulars of a register of civil status.

2/ Where the correction involves cancellation of word or number, the cancellation shall be carried out in a manner that the word or number remain legible.

3/ Where the correction affects all copies of the registration form, the officer of civil status shall give notice of same to all bodies which have already received such copies.

**50. Other Corrections**

Corrections in particulars entered in a register of civil status, other than those involving clerical mistakes, may not be corrected except by virtue of a judgment given by a court.

**51. Application for Correction**

An application for the correction of particulars entered in a register of civil status may be made to a court by the public prosecutor, officer of civil status or any interested person.

## ፶፪. የፍርድ ቤት ውሳኔ

፩/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የቀድሞው ምዝገባ እንዲታረም ወይም አዲስ ምዝገባ እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ ወይም አንቀጽ ፶፬ መሠረት እርማት እስከሚደረግ ወይም አዲስ ምዝገባ እስከሚከናወን ድረስ ውሳኔው ከክብር መዝገቡ ጋር እኩል ክብደት ያለው ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## ፶፫. የእርማት አመዘጋገብ

፩/ በመዝገቡ ውስጥ እንዲታረሙ የፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው መረጃዎች ከተሰረዙም በኋላ እንዲነበቡ ሆነው ይሰረዛሉ፡፡

፪/ በተሰረዙት ምትክ የሚገቡ ወይም ተጨማሪ ሆነው የሚገቡ መረጃዎች የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ በምዝገባ ቅጹ ጀርባ እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡

፫/ የክብር መዝገብ ሹሙ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጥቀስ የምዝገባ ቅጹ ቅጂዎች ቀደም ሲል የደረሷቸው አካላት ሁሉ እርማቱን እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡

## ፶፬. አዲስ ምዝገባ ስለማከናወን

፩/ በምዝገባው ላይ የሚደረገው እርማት ሰፊ ማስተካከያዎችን የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ምዝገባው ተሰርዞ በአዲስ ምዝገባ እንዲተካ ሊያዝ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አዲስ ምዝገባ ሲከናወን፦

ሀ) የቀድሞው የምዝገባ ቅጽ ተሰርዞ በጀርባው ላይ የፍርድ ቤቱን ውሳኔና አዲሱን ምዝገባ የያዘውን ቅጽ የሚያመለክት ማጣቀሻ ይሰፍራል፤

ለ) አዲሱን ምዝገባ በያዘው ቅጽ ጀርባ ላይ የፍርድ ቤቱን ውሳኔና የቀድሞውን ምዝገባ የያዘውን ቅጽ የሚያመለክት ማጣቀሻ ይሰፍራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት አዲስ ምዝገባ ሲከናወን፦

ሀ) የምዝገባ ቅጹ ቅጂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት መተላለፍ አለባቸው፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰው ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡



## 52. Judgment of Court

1/ The court may, upon examining the application submitted to it in accordance with Article 51 of this Proclamation, decide on the correction of the previous record or the drawing up of a new record.

2/ A judgment rendered pursuant to sub-article (1) of this Article shall have equal probative value as the register of civil status until the record is corrected or a new record is drawn up in accordance with Article 53 or Article 54 of this Proclamation.

## 53. Manner of Entering Corrections

1/ The particulars the correction of which is decided by the court shall be cancelled in the register of civil status, provided that they shall remain legible.

2/ The particulars which replace them or which are added in the register shall be entered on the back of the registration form, with a reference to the judgment of the court.

3/ The officer of civil status shall, with reference to the judgment of the court, give notice of the corrections to all organs which have already received copies of the registration form.

## 54. Drawing up a New Record

1/ Where the correction of a record entails substantial changes, the court may order the annulment of the record and the drawing up of a new record in its place.

2/ Where a correction is made pursuant to sub-article (1) of this Article:

a) the previous registration form shall be cancelled and a reference to the judgment of the court and the new record shall be made on its back side;

b) a reference to the judgment of the court and the previous record shall be made on the back side of the new registration form.

3/ Where a new record is drawn up pursuant to this Article:

a) copies of the registration form shall be sent to the relevant organs in accordance with Article 45 of this Proclamation;

b) a replacement certificate of registration shall be issued to the interested person in accordance with Article 47 of this Proclamation.

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለብሔራዊ መታወቂያ

### ፶፭. ስለብሔራዊ መታወቂያ ሰጪ አካል

ብሔራዊ መታወቂያ የመስጠት ሥልጣንና ተግባር የሚኖረው አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል፡፡

### ፶፮. ብሔራዊ መታወቂያ የማውጣት ግዴታ

፩/ ማንኛውም ለአካለ መጠን የደረሰ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ መታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ኢትዮጵያዊ ወላጅ ወይም አሳዳሪ ይህንኑ ልጅ በራሱ የቤተሰብ መዝገብ ላይ ማስመዝገብ አለበት፡፡

### ፶፯. ለብሔራዊ መታወቂያ ስለመመዝገብ

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፮(፩) መሠረት ብሔራዊ መታወቂያ የማውጣት ግዴታ ያለበት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በማስታወቂያ በሚገልፀው ቦታና ጊዜ መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ ምዝገባ የሚከተሉትን የተመዝጋቢውን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

- ሀ) ሙሉ ስም ከነአያት፤
- ለ) ልዩ ምልክት ካለ ይህንኑ ምልክት፤
- ሐ) የወላጆቹን ሙሉ ስምና ዜግነት፤
- መ) የትውልድ ቀንና ቦታ፤
- ሠ) ፆታና የጋብቻ ሁኔታ፤
- ረ) መደበኛ መኖሪያ ቦታና ሥራ፤
- ሰ) ብሔርና ሃይማኖት፤
- ሸ) ፎቶግራፍና የጣት አሻራ፤ እና
- ቀ) ሌሎች አግባብ ባለው የፌዴራል አካል የሚወሰኑ አስፈላጊ መረጃዎች፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሸ) ስለጣት አሻራ የተደነገገው ቢኖርም በአካል ጉዳት ምክንያት የጣት አሻራውን መስጠት የማይችል ሰው አግባብ ባለው ኃላፊ ፊት ቀርቦ ሌላ የማጣሪያ ዘዴ በመጠቀም ይመዘገባል፡፡

፬/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል የብሔራዊ መታወቂያ ለማግኘት የሚመዘገበውን ሰው ማንነት በጥንቃቄ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## CHAPTER THREE

## NATIONAL IDENTITY CARD

### 55. National Identity Card Issuing Organ

An appropriate federal organ having the powers and duties to issue national identity card shall be established by regulation of the Council of Ministers.

### 56. Obligations to Obtain National Identity Card

1/ Any Ethiopian who has attained majority shall have the obligation to obtain national identity card.

2/ Any parent or guardian of an Ethiopian minor shall cause the registration of such child on his family register.

### 57. Registration for National Identity Card

1/ Any Ethiopian who has the obligation to obtain national identity card in accordance with Article 56(1) of this Proclamation shall get registered at the place and within the period notified by the appropriate federal organ.

2/ The registration made in accordance with sub-article (1) of this Article shall contain the following information of the person registered:

- a) full name including grandfather;
- b) special identification, if any;
- c) parents' full name and citizenship;
- d) date and place of birth;
- e) sex and marital status;
- f) principal residence and occupation;
- g) ethnic origin and religion;
- h) photograph and finger print; and
- i) other necessary information as may be determined by the appropriate federal organ.

3/ Notwithstanding sub-article (2)(h) of this Article, a disabled person who cannot give his finger print shall be registered in the presence of the appropriate officer by other means of verification.

4/ The appropriate federal organ shall carefully ensure the identity of a person registering for national identity card.

፭/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል የተመዝጋቢውን ማንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ጥያቄዎችን የመጠየቅና ሊሟሉ የሚገባቸው ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፮/ ተመዝጋቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፶፰. <u>ብሔራዊ መታወቂያ ስለመስጠት</u>

፩/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯(፪) የተዘረዘሩትን መረጃዎች አሟልቶ ለሚያቀርብና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣው ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ መታወቂያ ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ብሔራዊ መታወቂያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ለተመለከተው ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ ሳይበላሽ እንዲያገለግል ሆኖ የተዘጋጀና ሚስጥራዊ መለያ ያለው ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) የባለመታወቂያውን ሙሉ ስም ከነ አያት፣ ፆታ፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ፣ ፎቶግራፍ፣ የጣት አሻራና ፊርማ፤

ለ) የብሔራዊ መለያ ቁጥርና የመታወቂያ ካርድ ቁጥር፤ እና

ሐ) የተሰጠበትንና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፡፡

፫/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል ብሔራዊ መታወቂያ ከመስጠቱ በፊት ተመዝጋቢው ግለሰብ አስቀድሞ ብሔራዊ መታወቂያ አለመውሰዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል የሚሰጠው ብሔራዊ የመለያ ቁጥር አስቀድሞ ለሌላ ዜጋ ያልተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፭/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በሚያስታውቀው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመመዝገብ ብሔራዊ መታወቂያ ያልወሰደ ኢትዮጵያዊ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ዘግይቶ በመመዝገብ መታወቂያውን ለመውሰድ በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተወሰነውን ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

## ፶፱. <u>ብሔራዊ መታወቂያ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜና እድሳት</u>

፩/ ብሔራዊ መታወቂያ ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአሥር ዓመት ይሆናል፡፡

፪/ ብሔራዊ መታወቂያ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ይታደሳል፡፡

5/ The appropriate federal organ shall have the power to make inquiries and to demand the production of relevant evidences to verify the identity of the person to be registered.

6/ The registered person shall confirm the veracity of the information provided in accordance with sub-article (2) of this Article.

## 58. <u>Issuance of National Identity Card</u>

1/ The appropriate federal organ shall issue a national identity card to an Ethiopian citizen who has furnished the full information specified under Article 57(2) of this Proclamation and effected payment of the service fee prescribed by regulation issued hereunder.

2/ A national identity card to be issued in accordance with this Article shall have the quality of lasting for the period of its validity referred to in Article 59 of this Proclamation, have security features and contain the following particulars:

a) the full name including grandfather, sex, date and place of birth, principal residence, photograph, finger print and signature of the holder;

b) national identification number and identity card number; and

c) issuance and expiry date.

3/ The appropriate federal organ, before issuing national identity card, shall ensure that the registered individual has not already received a national identity card.

4/ The appropriate federal organ, before assigning a national identification number, shall ensure that the number is not already assigned to another citizen.

5/ An Ethiopian who has not obtained a national identity card by getting registered within the period notified by the appropriate federal organ shall, unless he proves the existence of force majeure, be required to make payment of additional service fee prescribed by regulation issued hereunder, for issuance of the identity card upon late registration.

## 59. <u>Validity Period and Renewal of National Identity Card</u>

1/ A national identity card shall be valid for ten years from the date of its issuance.

2/ A national identity card shall be renewed upon the expiry of its validity period.

**፷. <u>የብሔራዊ መታወቂያ ያዥ ግዴታዎች</u>**

፩/ የብሔራዊ መታወቂያ ያዥ፡-

ሀ) መታወቂያውን በጥንቃቄ መያዝና ሁል ጊዜ ይዞ መንቀሳቀስ፣

ለ) በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ መታወቂያውን ማሳየት፣

ሐ) መታወቂያው በያዛቸው መረጃዎች ላይ ለውጥ ያጋጠመ እንደሆነ ለውጡን አግባብ ላለው የፌዴራል አካል በ፲፭ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ፣

መ) መታወቂያው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ አግባብ ላለው የፌዴራል አካል አቅርቦ ማሳደስ፣

አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ዜግነቱን የቀየረ ኢትዮጵያዊ የተሰጠውን ብሔራዊ መታወቂያ ወዲያውኑ አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መመለስ አለበት፡፡

፫/ ብሔራዊ መታወቂያው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፷፩ መሠረት የተሰረዘበት ሰው መታወቂያውን አግባብ ላለው የፌዴራል አካል መመለስ አለበት፡፡

**፷፩. <u>ስለብሔራዊ መታወቂያ መሰረዝ</u>**

፩/ ብሔራዊ መታወቂያ የተሰጠው በምዝገባው ወቅት በተሰጠ የተጭበረበረ ወይም የተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለመታወቂያው በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ መታወቂያው ይሰረዛል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መታወቂያው የተሰረዘበት ኢትዮጵያዊ እንደገና ተመዝግቦ ብሔራዊ መታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

**፷፪. <u>የብሔራዊ መታወቂያ መጥፋት ወይም መበላሸት</u>**

፩/ ብሔራዊ መታወቂያ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) መታወቂያው ስለመጥፋቱ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረጉን የሚገልጽ ማስረጃ፣ ወይም

ለ) የተበላሸውን መታወቂያ፣

በማያያዝ ምትክ ብሔራዊ መታወቂያ እንዲሰጠው አግባብ ላለው የፌዴራል አካል ማመልከት አለበት፡፡

**60. <u>Obligations of the Holder of National Identity Card</u>**

1/ The holder of a national identity card shall:

a) keep the identity card with care and always carry it with him;

b) show the identity card when requested by the concerned body;

c) inform the appropriate federal organ within 15 days of any change in the particulars of the identity card;

d) present the identity card to the appropriate federal organ for renewal upon the expiry of its validity period.

2/ Any Ethiopian who has changed his nationality shall forthwith return his national identity card to the appropriate federal organ.

3/ The person whose national identity card is cancelled in accordance with Article 61 of this Proclamation shall return the identity card to the appropriate federal organ.

**61. <u>Cancellation of National Identity Card</u>**

1/ Where it is proved that a national identity card is issued on the basis of fraudulent or false information provided during registration, the identity card shall be cancelled without prejudice to criminal liability of the holder.

2/ Any Ethiopian whose identity card is cancelled pursuant to sub-article (1) of this Article shall obtain a national identity card upon getting registered anew.

**62. <u>Loss or Damage of National Identity Card</u>**

1/ Any person whose national identity card is lost or damaged shall apply to the appropriate federal organ for issuance of a replacement upon attaching with his application:

a) in case of loss, an evidence of a report made to the police; or

b) in case of damage, the damaged identity card.

፪/ አመልካቹ በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣው ደንብ የተወሰነውን ክፍያ ሲፈፅም ምትክ ብሔራዊ መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

፫/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) የተመለከተው መረጃ እንደደረሰው የጠፋው ብሔራዊ መታወቂያ ለህገወጥ አገልግሎት እንዳይውል በማዕከላዊ መረጃ ቋት መጥፋቱን መመዝገብ አለበት፡፡

፬/ ብሔራዊ መታወቂያ ወድቆ ያገኘ ማንኛውም ሰው መታወቂያውን ወዲያውኑ አግባብ ላለው የፌዴራል አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ማስረከብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ተደራሽነት

### ፷፫. የመረጃ ልውውጥ

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባንና የብሔራዊ መታወቂያን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች አንዱ ለሌላውም የሚያገለግል መሆን እንዲችል አግባብ ባለው የፌዴራል አካል በማዕከላዊ የመረጃ ቋት በአግባቡ ተደራጅተው መያዝ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ እና አንቀጽ ፶፭ መሠረት የተቋቋሙ አግባብ ያላቸው የፌዴራል አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተያዙትን መረጃዎች መለዋወጥ አለባቸው፡፡

### ፷፬. ለሌሎች አካላት መረጃዎች ስለሚሰጡበት ሁኔታ

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወይም የብሔራዊ መታወቂያን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለሚከተሉት ዓላማዎች ሲባል ለሌሎች አካላት ተላልፈው ሊሰጡ ይችላሉ፡-

ሀ) ለብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፤

ለ) ለወንጀል መከላከልና ምርመራ ተግባራት፤

ሐ) ለግብር አሰባሰብ፤

መ) ለአስተዳደራዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች፤

ሠ) የፋይናንስ ተቋማትን የስጋት መቀነሻ ዘዴዎች በሥራ ላይ ለማዋል፤ እና

ረ) በሕግ መሠረት ለተፈቀዱ ሌሎች ዓላማዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መረጃዎችን ያገኘው አካል መረጃዎቹን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ወይም ለሌላ ዓላማ መጠቀም የለበትም፡፡



2/ The applicant shall be issued with a replacement national identity card upon payment of the fee prescribed by regulation issued hereunder.

3/ The appropriate federal organ shall, upon receiving the information referred to in sub-article (1)(a) of this Article, register the loss of the national identity card in the central data base to prohibit its illegal use.

4/ Any person who finds a lost national identity card shall immediately handover it to the appropriate federal organ or to the nearest police station.

## CHAPTER FOUR

## ACCESSIBILITY OF INFORMATION

### 63. Exchange of Information

1/ Information collected in relation to registration of vital events and national identity card shall properly be stored in a central data base kept by the appropriate federal organ so that the information collected for one purpose may also be used for the other.

2/ The appropriate federal organs established in accordance with Article 4 and Article 55 of this Proclamation shall exchange information kept in accordance with sub-article (1) of this Article.

### 64. Conditions of Disclosure of Information to Other Organs

1/ Information collected in relation to registration of vital events or national identity card may be disclosed to other organs for the following purposes:

a) for national intelligence and security services;

b) for crime prevention and investigation;

c) for tax collection;

d) for administrative and social services;

e) for implementation of risk management systems of financial institutions; and

f) for other purposes authorized by law.

2/ The organ which has obtained information pursuant to sub-article (1) of this Article may not disclose the information to other organs or use it for other purposes.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚመለከተው ግለሰብ ካልፈቀደ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር የግለሰብ መረጃዎች ለሌላ ሰው ተላልፈው አይሰጡም፡፡

፬/ በሚመለከተው ግለሰብ ፈቃድ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የግለሰብ መረጃ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም አለበት፡፡

፭/ የግለሰብን መረጃ ለሌላ ሰው መስጠት የሕዝብን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ሆኖ ሲገኝ መረጃው እንዲሰጥ የሚመለከተው ግለሰብ ቢፈቅድም መረጃው ለማንኛውም ሌላ ሰው መሰጠት የለበትም፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፷፭. የመረጃ አያያዝና ደኅንነት

፩/ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወይም ብሔራዊ መታወቂያን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን በሥርዓት ተደራጅተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ መረጃዎቹ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን በመጠቀም ከሚደርሱ ጥቃቶች፣ ከስርቆትና ከመሰል የወንጀል ጥፋቶች መጠበቅ አለባቸው፡፡

፫/ መረጃዎቹን የያዙ ሰነዶች ከተባይ፣ ከእሳት፣ ከእርጥበትና ጉዳት ሊያደርሱባቸው ከሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎች መጠበቅ አለባቸው፡፡

፬/ ሰነዶቹ ጽሑፎቻቸው እንዳይደበዝዙና ሌሎች ጉዳቶች እንዳይደርሱባቸው በቂ ብርሃንና አየር ባለበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡

### ፷፮. ቅጣት

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ወሳኝ ኩነትን የማስመዝገብ ወይም ብሔራዊ መታወቂያ የማውጣት ግዴታን ያላከበረ ወይም ከወሳኝ ኩነት ምዝገባ ወይም ከብሔራዊ መታወቂያ ጋር የተያያዘን ማንኛውንም ሌላ ግዴታ ያላከበረ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት መቶ ብር እስከ አምስት ሺ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, information specific to an individual may not be disclosed to any other person unless upon obtaining the consent of the concerned individual or an order of the competent court.

4/ A person entitled to obtain information specific to an individual by virtue of the consent of the individual or an order of the competent court shall be provided with the information upon payment of the service fee prescribed by regulation issued hereunder.

5/ Where disclosure of information specific to an individual is likely to prejudice public interest, such information may not be disclosed to any other person irrespective of the consent of the individual.

## CHAPTER FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 65. Handling and Safeguarding of Information

1/ Information collected in relation to registration of vital events or national identity card shall be kept properly to make them easily accessible for use.

2/ The information shall be protected from electronically designed attacks, theft or from other similar criminal abuses.

3/ Documents containing the information shall be protected against insects, fire, moisture and other causes of damage.

4/ The documents shall be kept in a place where there is sufficient air and light to protect written data from the risk of fading and other types of damages.

### 66. Penalty

1/ Whosoever:

a) fails to declare vital events or to obtain national identity card in accordance with the provisions of this Proclamation or fails to observe any other requirement provided for in relation to the registration of vital events or national identity card shall be guilty of an offence and be punishable with simple imprisonment not exceeding six months or with a fine from Birr five hundred to Birr five thousand;

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ወሳኝ ኩነትን ሲያስመዘግብ ወይም ለብሔራዊ መታወቂያ ሲመዘገብ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እውነተኛውን መረጃ የደበቀ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

ሐ) በሀሰት በተዘጋጀ ወይም ወደ ሀሰት በተለወጠ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ብሔራዊ መታወቂያ የተጠቀመ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

መ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ብሔራዊ መታወቂያ አስመስሎ የሰራ ወይም ወደ ሀሰት የለወጠ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሰባት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤ ሆኖም ጥፋቱ የተፈጸመው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ብሔራዊ መታወቂያ ለመስጠት ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ የሆነ እንደሆነ የጽኑ እስራት ቅጣቱ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል፤

ሠ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወይም ብሔራዊ መታወቂያን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ይዘት በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመሰረዝ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ወደ ሀሰት የለወጠ እንደሆነ ከአሥር እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

ረ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ወይም ብሔራዊ መታወቂያን አስመልክቶ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያደረገ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የወሰደ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከአሥር እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሌሎች ወንጀሎችን የፈጸመ እንደሆነ አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

## ፷፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚቋቋሙ አካላት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ተደራጅተው ሥራቸውን እስከሚጀምሩ ድረስ ወሳኝ ኩነትን እና የነዋሪነት መታወቂያ ካርድን በተመለከተ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ አካላት እየሠሩ ይቆያሉ፡፡



b) falsifies or conceals a fact in declaring a vital event or registering for a national identity card in accordance with this Proclamation shall be guilty of an offence and be punishable with simple imprisonment from one to five years;

c) makes use of forged or falsified certificate of registration of vital event or national identity card shall be guilty of an offence and be punishable with rigorous imprisonment from five to ten years;

d) forges or falsifies a certificate of registration of vital event or a national identity card shall be guilty of an offence and be punishable with rigorous imprisonment from seven to fifteen years; provided, however, that the rigorous imprisonment may extend up to twenty five years where the offence is committed by a civil servant or an official entrusted with the power to issue certificate of registration or national identity card;

e) falsifies data collected in relation to registration of vital events or national identity card by altering, modifying or deleting its content or by any other means shall be guilty of an offence and be punishable with rigorous imprisonment from ten to twenty five years;

f) damages, destroys, suppresses or unlawfully accesses the data collected in relation to registration of vital events or national identity card shall be guilty of an offence and be punishable with rigorous imprisonment from ten to twenty five years.

2/ Whosoever commits other offences in violation of the provisions of this Proclamation shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

## 67. Transitory Provisions

1/ Existing organs providing services relating to registration of vital events and issuance of residential identity cards shall continue functioning until the organs to be established for the implementation of this Proclamation becomes operational within a period not exceeding two years from the effective date of this Proclamation.

፪/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት የተከናወኑ የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎችና የተሰጡ ማስረጃዎች ጸንተው ይቆያሉ፡፡

፫/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት የተሰጠና ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜው ያላለፈ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ በብሔራዊ መታወቂያ እስከሚተካ ድረስ አገልግሎት መስጠት ይቀጥላል፡፡

፬/ በሥራ ላይ በነበሩ ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች መሠረት ሳይመዘገብ የቆየ ወሳኝ ኩነት የሚመለከተው ሰው ደጋፊ ማስረጃዎችን አያይዞ ሲያመለክት በዚህ አዋጅ መሠረት ተመዝግቦ ለአመልካቹ የወሳኝ ኩነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፷፰. **የተሻሩ ሕጎች**

፩/ በ፲፱፻፶፪ የወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፵፯ እስከ አንቀጽ ፩፻፶፫ ያሉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፷፱. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ አግባብ ያለው የፌዴራል አካል ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፸. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Vital events registered and certificates issued on the basis of the existing laws or customary practices shall remain valid.

3/ A residential identity card issued on the basis of the existing laws or customary practices, and the period of validity of which has not expired, shall remain valid until replaced by a national identity card.

4/ A vital event not registered on the basis of the existing laws or customary practices shall, upon application of the interested person accompanied by a supporting evidence, be registered in accordance with this Proclamation and a certificate of registration of vital event shall be issued to the applicant.

68. **Repealed Laws**

1/ The provisions of the 1960 Civil Code from Article 47 to Article 153 are hereby repealed..

2/ No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

69. **Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulation necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The appropriate federal organ may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulation issued in accordance with sub-article (1) of this Article.

70. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of August, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**